## በመንግስት ላይ የቀረበ ትዝብት

### *ትዝብት አንድ ጠቅላላ እይታ*

ከኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ በግልፅ እንደምንረዳው በቅድሚያና ትኩረት የሚሰጠው የወንጀል ድርጊት እንዳይፈፀም በመከላከል ድረጊቱን ሳይፈፀም ማሰቀረት ነው።ይህን ዓላማ ለማሳካት መንግስት ያለበትን ሃላፊነት በአግባቡ መወጣት ና ይህን ሃላፊነት ለመወጣት የፍትህ አካላትን ጨምሮ የተለያዩ የፀጥታ አካላትን መጠቀም ይኖርበታል። ለነገር ግን ሁሉንም አይነት የወንጀል ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ መከላከል ባይቻልም በማን አለብኝነትና በአደባባይ የሚፈፀሙትን ግን መከላከልና ማስቀረት ይቻላል።አንድ የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመ በኃላ በህግ ስርዓት አጥፊውን በመለየት አጣፊውን ሊያስተምር የሚችል እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ መሰል የሆነ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈፅሙ የሚያስተምርና የሚያስጠነቅቅ ቅጣት መሰጠት ይኖርበታል።

በአንድ ሃገር ወሰጥ ህገ መንግስታዊ ስርዓት አለበት በሚባልበት ሁናቴ ዜጎች በሰላማዊ ሁኔታ ና ያለስጋት የመኖር መብት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ ይህን የመኖር መብት ደግሞ የመጠበቅና የማስጠበቅ ዋነኛው የመንግስት ሃላፊነት ነው።

ከዚህ አንፃር በሰሞኑ በሃገራችን ኢትዮጵያ የተፈጠረውን ዘግናኝና አሰቃቂ ድርጊት ስንመለከት በአንድ ሃገር ውስጥ መንግስት እያለ ጠንካራ የፀጥታ መዋቅር አለ በሚባልበት ሁኔታ(በመንግስት እይታ) የተወሰኑ ቡደኖች የአንድን ብሄር የማይወከሉ የፈለጉትን ድርጊት ሲፈፅሙና ሲያደርጉ ቁጭ ብሎ ማየትና መመልከት ለድርጊቱ ዕውቅና መስጠት በመሆኑ እንደ መንግስት ከማሳፈሩም በላይ ውድቀት ነው።የሰውን ልጅ ያህል ፍጡር በቢላዋ ሲያርዱ፣ምላስ ሲቆርጡና እንደ ከብት ቆዳ ገፈው ሲሰቅሉ መመልከከት ድርጊቱን ከመፈለግ ባለፈ መክሸፍና መውደቅ ሲሆን አንድ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈፀም ማሰቀረትና መከላከል እየተቻለ ድርገቱ ከተፈፀመ ቧኃላ ፖለቲካዊ መልስ መሰጠት ደግሞ ህዝብን መናቅ ነው።

ከስህተቱ የማይማረው ፈንጅ አምካኝ ብቻ ነው እነደሚባለው በጥቅምት ወር 2012 ዓም በኦሮሚያ ክልል በተፈፀሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና የንብረት መውደም በሌላ ጊዜና ቦታ እንዳይፈፀም አለመጠንቀቅ ና አለመከላከል ከእንዝላልነት ባለፈ በማንና ምን አለብኝነት የታለፈ በመሆኑ በህግ ያስጠይቃል።ስለዚህ መንግስት ካለፈው ስህተቱ ሳይማር መቅረቱ የፈንጅ አምካኙ ዕጣ ፈንታ እንደ ሚደርሰው ማወቅ ይገባዋል።

መንግስት ያለበትን ግዴታና ሃላፊነት ሳይወጣ ሲቀር ተጠያቂ ሊያደረገው የሚችል ጠንካራ የፍትህ ተቋም መኖር ያስፈልጋል።በዚህም መሰረት መንግስት ያለበትን ግዴታና ሀላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ገለልተኛ የሆነ የፍትህ አካላት( ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ ና ፖሊስ) ድርሻ የጎላ ነው። ይህም ሲባል መንግስትም ቢሆን ባጠፋው ልክና ባለበት ሃላፊነት መጠን ተጠያቂ ሊያደርገው የሚችል የፍትህ ስርዓት መኖር አለበት። ጠንካራ የፍትህ ሰርዐት ሲኖር ተጠቃሚ የሚሆነው ህዝብ ብቻ ሳይሆን መንግስት ራሱ ያሉበትን ሃላፊነቶች በአግባቡና ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መፈፀም ያስችለዋል።

የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን በተመለከተ ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለያዩ ሃገራት በሃገራቸው የህግ ማዕቀፉ ወስጥ ያካተቱ ሲሆን ለምሳሌ ያህል ከመንግስት ግዴታዎች ውስጥ ዜጉቹን ከሰጋት መከላከልና ማህበራዊ አገልግሎቶችን የማቅረብ ግዴታ ይገኝበታል። ይህም ማለት መንግስት ስልጣን ይዞ በሚመራበት ሃገር ዜጎች ግብር የሚከፍሉት መንግስት ያለበትን ሃላፊነት በአግበቡ እንዲወጣና ለመሰረተ ልማት አገልግሎት እንዲያውልና በኢኮኖሚ የጎለበተ ሆኖ ህዝቦችን በእኩልነት ያለ አንዳች ልዩነት እንዲያገለግል ነው እንጅ በሽብርተኛ ቡድኖች ህይዎቱ ሲቀጠፍና ንብረቱ ሲወድም ቁጭ ብሎ እነዲመለከት አይደለም። ስለሆነም ህገመንግስታዊነት በሌለበት ሃገር በህገመንግስት ውስጥ የተለያዩ የሰብዓዊ ና ደፀሞክራሲያዊ መብቶችን ማካተት ትርጉም የለፀለው ስለሆነ መንግስት ለእነዚህ መብቶች ተግባራዊነት መስራት ይኖርበታል።

በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች በዋነኝነት በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ሰፍራዎች በተዎሰኑ ቡድኖች የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና የንብረት ውድመት ዘግናኝና አሰቃቂ ከመሆናቸውም ባለፈ ዘመናትን የሚሻገሩና ለ ቀጣይ ትውልድም ቢሆን ከፉ ጠባሳ የሚያሳርፉ እኩይ ተግባራት ናቸው።በተለይም የመንግስት የፀጥታ መዋቅር በተዘረጋበት አካባቢ ይህን የመሰለ ድርጊት መፈፀሙ ከማሳዘኑ በተጨማሪ የመንግስትን መኖርና ስልጣኑን በእውነትም እየተገበረ ሰለመሆኑ ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ነው። በአርሲ ነገሌ፣ በዝዋይና በሻሸመኔ የተፈፀሙትን እኩይ የሰብዓዊ መብት ድፍጠጣዎች እና የንብረት ውድመት የአንድን ብሄር ማንነት የሚወክል ተግባር ባለመሆኑ ሁሉም ያለምንም የዘርና ማንነት ልዩነት ሊያወግዙት የሚገባ ድርጊት ነው።

ሰለሆነም በኦሮሚያ ክልል ለተፈፀሙ ማናቸውም አይነት ድርጊቶች መንግስት ያለበትን ሃላፊነት ባለመወጣቱ ምክንያት የተፈጠሩ በመሆናቸው ፣ድርጊቱ እንዳይፈፀም መከላከል እየተቻለ ና የማስቀረት መሉ አቅም እያለው ይህን ባለማድረጉ ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል የ ጅምላ እስር ማድረግ ከሚያሰተቸውና ተጠያቂ ከሚያስደርገው በቀር ሊመሰገንበት የሚገባ አንዳችም ምክንያት የለም። በመሆኑም ለተፈፀሙየት አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችና ለጠፋው ውድ የሰው ህይዎት ዋነኛውና የመጀመሪያው ተጠያቂ መንግስትና የመንግስትን ስልጣን የያዙ ግለሰቦች በመሆናቸው መንግስት ለጠፋው ውድ የሰው ህይዎት የሚተካ ባለመሆኑ ሃላፊነቱን በመውሰድ የድርጊቱን ፈፃሚዎች በመለየት ተጠያቂ ማድረግ፣ ለወደመው የዜጎች ንብረት መልሶ የማቋቋና መሰል ድርጊቶች ወደፊት እንዳይፈፀሙ ለህብረተሰቡ ከለላ በማድረግ የዜጎዘችን የመኖር መብትና ሃብት የማፍራት መብት የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታዎች ሊወጣ ይገባል።

መንግስት በሃገር ውስጥ በሰሞኑ የተፈጠሩ ግጭቶችን መከለከልና ማስቀረት ያልቻለ ፣የዜጎችን በህይዎት የመኖር መብታቸውን ያላረጋገጠ፣በተወሰኑ ቡድኖች የተፈጠረን ማን አለብኝነት ማስቆም ካልቻለ  እንዴት ነው የውጫ ወራሪ ሃይል ቢመጣና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቢፈፅም መንግስት  ዜጎቹን የመጠበቅ ግዴታውን ሊወጣ የሚችለው?

### *ትዝብት ሁለት*  ስለ እስክንድር

እስክንድር ማለት በእኔ አገላለፅ  መንግስት የጣላቸውን  እና ያነሳቆላቸውን እንዲሁም  መኖራቸውን የረሳቸውን በማስታወስ በሃገራቸው ውስጥ የመኖር መብት  ያላቸው መሆኑን ያሳወቀ፣ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ  ቢሆን መብትን መጠየቅን ያስተማረ  ብሄራዊ ጀግና ነው።እስክንድር የግል ህይወቱን ትቶ ትዳሩና ልጁን ረስቶ በእስር የሚንገላታውና በድብደባ የሚሰቃየው ለ ዲሞክራሲና ለህግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብት መከበር በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ የዲሞክራሲ ስርዓት እንዲያገኝና የህግ የበላይነት እነዲረጋገጣለት የከፈለውን ዋጋ ማንም አልከፈለም። አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት  እስክንድርን ለማሰር፣ለመደብደብና ለማንገላታት  ምንም አይነት የሞራል ልዕልና የለውም። በቅድሚያ መንግስት ከእስክንድር መማር የነበረበት  የኢትዮጵያን ህዝብ ማገልገል፣ለህዝብ መቆም፣የዲሞክራሲና የህግ የበላይነትን ን ለህዝቡ ማረጋገጥ፣የሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ መከላከል ነው እንጅ እስክንድርን በሄደበት ቦታ እየተከተሉ  ማሰቃየት የሽንፈት ጥግ ነው።እየተገፋ የሚያኮራ፣ እየታሰረ የሚያሸንፈው ፣ ለቆመለት ዓላማ ወደ ኃላ የማይል፣ለመታሰር ብቻ ሳይሆን ለመሞትም ዝግጁ የሆነ ጀግና ኢትዮጵያዊ ነው። የመንግስትን ያልተገባ አሰራርና አድሎዓዊነት የሚታገለው ሸሽቶ ሳይሆን ፊትለፊት ቆሞ ደረቱን ለመሳሪያ ሰጥቶ ነው።እስክንድርን ማስር፣መደብድብና ማንገላታት እንዲሁም በላዩ ላይ የክስ ናዳ ማዥጎድጎድ   እስክንድርን ከቆመለት ዓላማ አያስቆመውም።

በጥቅምት ወር 2012 ዓም  በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ከተሞች ዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ሲታረዱና ሲገደሉ ምንም አይነት እርምጃ መውሰድ የሚችለው መንግስት ዝምታን መርጦ   በፌደራሉ መንግስት መቀመጫ በሆነችው አዲስ አበባ በኦሮሚያ ከተማ የተፈጠረውን አሰቃቂ ድርጊት በድጋሜ እንዳይፈጠር ህዝቡ ራሱን እንዲጠብቅ ግንዛቤ ፈጠረ ቢባል እንኳ በወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችል የሞራል ኢለመንት የለውም። ህዝብ የሚኖርበትን ከተማ ለዚያውም የፌደራሉ መንግስት መቀመጫ የሆነው ከተማ ላይ እንደዚህ አይነት ድርጊት ሲፈፀም እንደ መንግስት አግድሞ መመለከት  አንድም ድርጊቱ እንዲፈፀም ፍላጎት አለ ወይም ደግሞ ፀጥታውን የማስከበር አቅም ችግር አለ ማለት ነው።ሌላው የሚገርመው ነገር  እስክንድር ቀድሞ ማህበረሰቡ ራሱን ከጥቃት እንዲከላከል  ህዝቡን ቀሰቀሰ ቢባልም  እንኳ የፈጠረውን ግንዛቤ  በኃላ ላይ  የፌደራሉ ፖሊስ ኮሚሽን  ተመሳሳይ መልዕክት ማስተላለፉ ብቻ ሳይሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ  ራቸው  ማህበረሰቡ በንቃት ራሱን እንዲከለከል መክእከት ማስተላለፋቸው ነው።

በጣም ከሁሉም በላይ የሚገርመው ጉዳይ  በአዲስ አበባ ከተማ  ከተለያየ ቦታ የመጡ  የአሸባሪ ቡድኖች ምክንያት   ጥቃትና ውድመት  ሊደርስ እንደሚችል እስክንድር ቀድሞ ተረድቶ  ህዝቡ ራሱን እነዲከላከል አንቅቷል ቢባልም  ፣ መንግስት ድርጊቱ እንዳይፈፀም ማሰቀረትና መከላከል አየቻለ  ድርጊቱን አለማስቀረት ምን አይነት የመንግስትነት ባህርይ ነው?

ሌላው እስክንድር የፖለቲካ ፓርቲ መሪ እንደመሆኑ መጠን የመንግስትን አሰራር  በመገምገም መተቸትና  የመንግስትን ህፀፅ ለህዝብ ማሳወቅ ዋነኛ ተግባሩ ነው። ስለዚህ  እስክንድር የሚናገረውንና የሚተቸውን  መፍትሄ ከመሰጠት ይልቅ እየለቀሙ የወነጀል ድርጊት ማሰመሰል ሃገሪቱ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዳትጀምር ዋነኛ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ በለውጥ ስም  የመጣው  ሃይል   በሃገራችን ኢትዮጵያ  የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዳይጀመርና እንዳያብብ ያለውን ፍላጎት ማሳያ ነው።

እስክንድር  በወንጀል ተጠርጣሮ በፖሊስ ተያዘ ማለት የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል ማለት አይደለም።ከዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ እስክንድር በፖሊስ የተያዘው በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ እንጅ የወንጀል ድርጊት ሰለፈፀመ  ባለመሆኑ በየሚድያው የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ የስራ ሃላፊዎችና  የፌደራል ፖሊስ  የስራ መሪዎች  እየወጡ እስክንድር የወንጀል ድርጊት  ፈፅሞ ነው   የታሰረው በማለት የሚሰጡት መግለጫም ሆን ማስደነገጫ  የእስክንድርን ነፃ ሆኖ የመገመት መብት(presumption of innocence) የሚጻፈጥጥ አካሄድ ነው።   እስክንድር የተያዘው የኢትዪጵያን ህዝብ ለማስደንገጥና  ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ህወሓት ሲፈፅመው የነበረውን ህዝብን የማስበርገግ ተግባር በመሆኑ፣ ህዝቡም ቢሆን በእስክንድር መታሰር የማይደናገጥና እስክንድር ያስጀመረውን ትግል የሚያስቀጥል  በመሆኑ፣ መንግስት ያሰረውም የእስክንድርን አካል እንጅ  የሞራል ልዕልናውና ዓላማውን ባለመሆኑ፣  እስክንድር ብሄርን ከብሄር  ዘርን ከዘር የሚያጋጭ የሞራል ዝቅጠት የሌለበት በመሆኑ፣ እስክንድር የታሰረውና በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ እየተሰራ ያለው  ለማሙያነት እንጅ የ ወንጅል ድርጊት ስለፈፀመ ባለመሆኑ፣ እስክንድር የተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ህግ(ድርጊት) በመርህ ደረጃም ይሁን በልዩ ሁኔታ የዋስትና መብቱን ሊያስነፍገው የሚያስችል ምክንያት ባለመኖሩ፣ መንግስት በአፋጣኝ እስክንድርን ከእስር  ሊፈታው ና   ከእስር ከተፈታም በኃላ መንግስት ተገቢውን ጥበቃ ሊያደርግለት ይገባል።

### *ትዝብት ሶስት*   በኦሮሚያ ክልል በማንነታቸው ምክንያት የተገደሉ ዜጎችን በተመለከተ

በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ከተሞች  ማለትም በዝዋይ፣በኔጌሌ፣እና በሻሸመኔ የተከሰቱ ዘግናኝ ድርጊቶች የተከሰቱት በክልሉ የስራ ሃላፊዎች ድክመት እና በፌደራሉ መንግስት  ዳተኝነት ነው ። የኦሮሚያ ክልል መንግስት በጥቅምት ወር 2012 ዓ ም በተፈጠሩት ክስተቶች ሳይማር ና ሳይጠነቀቅ  ተመሳሳይ ድርጊት በክልሉ ሊፈፀም እንደሚችል በመገመት ቅድመ ጥንቃቄ ሊያደርግ ሲገባው  ይህን ባለማድረግ  ለጠፋው የሰው ህይዎትና ለወደመው ንብረት የኦሮሚያ መንግስተ ድርሻ የጎላ ነነው።በእውነት የኦሮሚያ ክልል መንግስት

የተከሰተው ችግር እነዳይፈጠር ፈልጎ ቢሆን ኖሮ  እና  እነዚህና መሰል ድረጊቶችን የመከላከልና የመቆጣጠር አቅም ችግረ ካለበት የፌደራል መንግስቱን ጣልቃ ገብነት መጠየቅ ይችል ነበር ።

በአዋጅ ቁጥር 359/1995 መግቢያ ላይ በግልፅ  እንደተቀመጠው የፌደራሉም መንግስት ቢሆን፣  የክልሉ መንግስት የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ባያቀርብለትም  በህገ መንግስቱ አንቀፅ  51 ንዑስ አንቀፅ 1 ፣አንቀፅ 51 ነዑስ አንቀፅ 14፣አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 16  እና አንቀፅ 62 ንዑስ አንቀፅ  9 መሰረት በፌደራሉ መንግስት ምክር ቤቶች ጥያቄና በራሱ በፌደራል መንግስቱ ተነሳሽነት ጣልቃ መግባት እንደሚችል የተደነገገው።   ከዚህ መረዳት የምንችለው  የኦሮሚያ ክልል  በክልሉ የሚኖሩ ሁሉም ዜጎች ደህንነትና ህይዎት ካሳሰበው አንድም በራሱ የክልሉ የፀጥታ መዋቅር ፣አሊያም ደግሞ የ ፌደራል መነግስቱን ጣልቃ ገብነት በመጠየቅ  የተፈጠረውን ችግር ማስቀረትና መከላከል እየተቻለ  የክልሉ የስራ ሃላፊዎች ይህን ባለማድረጋቸው  ለደረሰው ጉዳት  የመጀመሪያ ተጠያቂዎች ናቸው ። በለላ በኩል የፌደራሉም መንግስት ቢሆን በራሱ ተነሳሽነት በክልሉ ጣልቃ በመግባት የዜጎችን ህይዎት  ከሞት መታደግና ንብረታቸውነም ቢሆን ከውድመት ማትረፍ  እየቻለ ይህን ግዴታ ሳይፈፅም በመቅረቱ ጉዳት የደረሰ ሰለሆነ የፌደራሉ መንግስት ሃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት።

በጣም የገረመኝና ያሳዘነኝ ጉዳይ  በኦሮሚያ ክልል  በተለያዩ ከተሞች  በብሄራቸው ምክንያት ለተገደሉ ዜጎች ቤተሰቦች እውቅና አለመስጠት ነው ።በክልሉ በደረሰባቸው ጥቃት ምክንያት  ህይዎታቸውን ያጡ 239  ዜጎች(መንግስት ባመነው መሰረት) ምንም አይነት እውቅና ሳይሰጥና ብሄራዊ  የሀዘን ቀን ሳይታወጅ  መቅረቱና ለሃጫሉ ሞት ብቻ ትኩረት ሰጥቶ  የሀዘን ቀን  ማወጅ ነው። እዚህ ላይ ያለኝ ቅሬታ  ለሃጫሉ ለምን የሃዘን ቀን ታወጀ ሳይሆን  ሌሎቹም የሞቱ ግለሰቦች እንደ ሃጫሉ  የሃዘን ቀን ሊታወጅላቸው የሚገባ በመሆኑ ይህም ሲባል የሃዘን ቀን መታወጁ ለሞቱት ሰዎች ሰለሚጠቅማቸው ሳይሆን በህይዎት ላሉት ቤተሰቦቻቸው መፅናኛ ከሚሆናቸዉ በቀር ምንም አይነት ፋይዳ የለውም። ስለዚህ የሃጫሉም ሞት ቢሆን የከፈለዉ ዋጋ እንዳለ ሆኖ    እንደ አንድ ግለሰብ ተቆጥሮ 240 ኛ ሟች    ሆኖ መጠራት  ሲገባዉ በየሚድያው  ሃጫሉና 239  ሰዎች እያሉ መጥራት በህይዎት ለተረፉት ለሟች ቤተሰቦች ንቀት ከመሆኑም በላይ የማይሽር ህመም ነው።

በጥቅሉ በኦሮሚያ ክልል ለተፈፀሙት  ጉዳቶች ተጠያቂው  የኦሮሚያ ክልል መንግስትና የፌደራሉ መንግስት  ሆነው ሳለ ፣   በክልሉ በማንነታቸው ምክንያት  ለሞቱት ዜጎችና ቤተሰቦች እውቅና አለመሰጠት፣ለአንድ ግለሰብ ሞት የሀዘን ቀን ሲታወጅ የ239  ዜጎችን ሞት ከምንም መቁጠር፣ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚች ቤተሰቦችና ንብረት የወደመባቸውን ግለሰቦች    አድረስ አለማድረጋቸውና ለድረጊቱ ዘግይተው መግለጫ ማውጣታቸወን ሰንመለከት ከጊዜ ጊዜ እየለመድን ለመጣነው ሞት ቀጣይም ቢሆን ሌሎች ተረኛ ሟቾችን እንድንጠብቅ ከማድረግ ውጫ ሌላ ፋይዳ የሌለዉ  መሆኑን  ከሰሞኑ የታዘብኩት ክስተት ነው።

***ትዝብት አራት        የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ህግን በተመለከተ***

በኢትዮጵያ የፍትህ ስርዓት ውስጥ  ፍርድ ቤት፣የዓቃቢ ህግ ቢሮና የፖሊስ ተቋማት ዋነኞቹ ናቸው። የአንድን ሃገር የፍትህ  ስርዓት ለማጎልበት እነዚህን ተቋማት ነፃና ገለልተኛ ከማድረግ በተጨማሪ ማዘመንም አስፈላጊ ነው። የሶስቱም አካላት ስልጣንና ተግባር የተለያየ ቢሆንም ፍትህን ለዜጎች በማድረስና በማረጋገጥ ረገድ  ግን   አንድ አይነት ናቸው።  ፖሊስ ከማህበረሰቡ የሚደርሰውን የወንጀል ጥቆማ በመቀበል ወይም በራሱ ተነሳሽነት የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን የተረዳ እንደሆነ ፣ አንድን ተጠርጣሪ አስይዞ ምርመራ ሊያስጀምር የሚችል ማስረጃ ያገኘ እነደሆነ፣ ምርመራውን በማድረግና በማጣራት የምርመራ መዝገቡን ለዓቃቢ ህግ በማቅረብ፣ ዓቃቢ ህግም የቀረበለትን የምርመራ መዘገብ  በማየትና በመመርመረ  ሊያስከስስ የሚችል ወይም ደግሞ ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችል ማስረጃ ያለው እንደሆነ  ክስ በማዘጋጀት ለፍርድ ቤት በማቅረብ  የፍረድ ሂደቱን መከታተል ያለበት ሲሆን፣ ፍርድ ቤትም እንደ  ስራ ድርሻው የቀረበለትን ክስና ማስረጃ ከህጉ ጋር በማገናዘብና በመመረመር  ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያሰብል የሚችል ማሰረጃ ያገኘ አንደሆነ ጥፋተኛ ማለት አሊያም ደግሞ  ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረጃ ያልቀረበ እነደሆነ ተከሳሹን በነፃ መልቀቅ ዋነኛና  ብቸኛ ተግባራቸው ነው።

በሰሞኑ በኢትዮጵያ  በአዲስ አበባና በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የተከሰተውን  ክስተት አሰመልክቶ  የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል። በዚህም መሰረት  ከሰኔ 29 ቀን 2012ዓም  ጀምሮ ባሉት  የተለያዩ ቀናት  ሰለ እሰክንድርና ጃዋር ሙሐመድ  የተለያዩ መግለጫዎች ተሰጥተዋል።

ዋና ጠቅላይ ዓቃቢ ህጓ እስክንድርንና የስራ ባልደረቦቹን በተመለከተ አዲስ አበባ  ላይ ቄሮ ሊፈጅህ ነው  በሚል ብሄር ተኮረ ጥላቻዎችንና የተለያዩ መልዕክቶችን በመስጠት የአመፅ እነቅስቃሴው እንዳይቋረጥና ቀጣይ እንዲሆን ፣የሃገርን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ስራ ሲሰሩ እነደነበር መረጃ እንዳለዎት ፣ እንደውም የነእሰክንድርና ሌሎች በሶስቱ ሰኔዎች ችግር ሊፈጥሩ ካሰቡ ሃይሎች ስራዎች ጋር ትስስር እንዳለው በገደምዳሜ ጠቁመውናል።ይህ የአብዪን ለእምዪ መስጠት መንግስትዎ ቀደም ብሎ የነጃዋር ቡድን የሰኔ ላይ ይለያል ድግስ አዘጋጅቶ እንደነበር ከነገረን ታሪክ ጋር ይጋጫል።አሁን ደግሞ የዚህ ድጋስ ባለቤት ባልደራስም ነበር ሲሉን የሞራልም የአመክንዮም ችግርን ያሳብቃል።( ፍትህ መፅሄት    ረቂቅ ይሁን ሃምሌ 2 ቀን 2012 ዓም

በዝዋይ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉት የአንድ ቤተሰብ አባላት ( ወ/ሮ ፀሃይ መንግስቱ ቀፀላ፣አቶ ገለታው አውላቸው፣ወጣት ነፃነት ገለታው አውላቸው፣ወጣት ሳሙኤል ገለታው አውላቸው ና ወጣት ዋስይሁን አግዜ)  ዘመዶችን ከጋዜጠኞች ጋር እንኳን እንዳያወሩ ማሰፈራራያ የሚሰጥ  ቡድን በኦሮሚያ  በሚያንጥብበት ሁኔታ ህዝቡን ደፋር ሁን ማለት ብቻ ድፍረት አያመጣም መተማመኛም

አይሰጥም። የህዝብ ፍርሃት የመንግስት ፀጥታንና የህግ የበላይነትን ማስከበር አለመቻል ማሳያ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።የተወሰኑ የመንግስት ባለስልጣናት የብሄር ተኮሩ ጥቃት ተባባሪ ናቸው ብሎ የሚያምን ህብረተሰብን፣የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች አድሎአዊ ወገንተኝነት በሚያሳዩበት ሁኔታ ፣ መንግስት ተመሳሳይ ብሄር ተኮር ጥቃቶችን የፈፀሙ ሰዎችን ታማኝ በሆነ ህግን በተከተለ የፍርድ ስርዓት ተጠያቂ የማድረግ ፍላጎትም ልምድም የሌለው መንግስት ህዝብን ፈሪ አትሁን ብሎ መመከር የራሱን ፈሪነትና ልፍስፍስነት ከማሳየት ያለፈ ፋይዳ የለውም።( ፍትህ መፅሄት ቂቅ ይሁን ሃምሌ 2 ቀን 2012 ዓም)

የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ (የቀድሞው ፍትህ ሚኒስቴር) በአዋጅ ቁጥር 943/2009 ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በፌደራሉ መንግስት ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የሚያርፉ የወንጀል ድርጊቶችን በተመለከተ ምርመራ ከማስጀመር ጀምሮ የምርመራ መዝገብ እስከማቋረጥ ድረስ ስልጣን የተሰጠው ለዋና ጠቅላይ ዓቃቢ ህጉ ነው(ለሚንስትሩ እንደማለት ነው)። ይህም ዋና ጠቅላይ ዐቃቢ ህጉ የፌደራል መንግስቱ የካቢኔ አባል እንደመሆኑ መጠን ፣በተቋሙ የሚሰሩ የፖለቲካ ይዘት ያላቸውን የምርመራ መዝገቦች ከመሪዉ የፖለቲካ ፓርቲ ፍላጎት ወጭ ገለልተነኛ የሆነ ውሳኔ ሊወስን እንደማይችል እሙን ነው። ሌላው በጣም የሚገርመው ጉዳይ በዚህ አዋጅ ውስጥ ዓቃብያነ ህጎች ምንም አይነት የፖለቲካ አመለካከት እንዳያነፀባረቁ መከልከሉ ነው። ዋና ዓቃቢ ህጉ ምንም አይነት ውሳኔ የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶት እያለ ተራ ዓቃብያነ ህጎችን የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አለመቻል ብቻ ሳይሆን ማንኛውነም አይነት የፖለቲካ አመለካከት እንዳያንፀባርቁ መከልከል ለይስሙላ ተቋሙን ገለልተኛ ለማስመሰል የተደረገና በሰሞኑ የተፈጠሩት አይነት ክስተቶች ሲያጋጥሙ የተቋሙን የስራ ድርሻ በገለልተኛ ዓቃቢ ህጎች እንደተሰሩ ከማስመሰል ውጭ ፋይዳው ምንድን ነዉ?

ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ጠቅላይ ዓቃቢ ህጉ የፌደራሉ መንግስት ዋና የህግ አማካሪ እና የካቢኔ አባል ሆኖ (ከአስፈፃሚው አካል ጋር አብሮ ተቀምጦ የወሰነውን ውሳኔ) እየሰራ ባለበት ሁኔታ ነፃና ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ ሊወስን ይችላል ብሎ መጠበቅ ከበሬ ወተት እንደመጠበቅ ነው። ለዚህም እንደ አንድ ማሳያ ሊሆን የሚችለው የአርቲስት ሃጫሉን ግድያ በተመለከተ የተጠረጠሩ ግለሰቦችን በተመለከተ የወጣው መግለጫ ሁለት አይነት ይዘት አለው ።በመጀመሪያዉ መግለጫ ከአርቲስቱ ግድያ ጋር የተጠረጠሩት ግለሰቦች አምስት እንደሆኑና አራቱ በቁጥጥር ስር እንደዋሉ የሚገልፅ ሲሆን ሌላዉ ደግሞ አጠቃላይ ተጠርጣሪዎች ሶስት እንደሆኑና ሁለቱ ተይዘው ሶስተኛው እየተፈለገ መሆኑን የሚገልፅ መግለጫ ነው። ስለ መጀመሪያዎቹ ተጠርጣሪዎች(ወንጀለኛ ተብለው የተገለፁት) ምንም ሳይባል ሌሎች ወንጀለኞች(ተጠርጣሪዎች መባል ሲገባው) ተገኙ ብሎ መናገር በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የፈለገውን ነገር ማድረግ እነደሚችልና ህዝብ ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችል ማሳያ ነው።

ሌላው የጠቅላይ ዓቃቢ ህግ አስነዋሪ ተግባር ነፃ ሆኖ የመገመት መብትን (presumption of innocence) ረስቶ እንደ ወንጀለኛ መቆጠር ((presumption of guilty) ማስፈኑ ነው። የአንድ ተቋም መሪ ለዚያዉም ጠቅላይ ዓቃቢ ህግን ያህል ተቋም እየመሩ ፣ የህግ ትምህርት ቤት ገብቶ ህግ የተማረ ሰው(ዋና ጠቅላይ ዓቃቢ ህጓ ህግ ባይማሩ ኖሮ ተቋሙን እንዲመሩ አይደረግም ነበር በማለት አስቤ ነው) ፣ስለ ተጠርጣሪና ወንጀለኛ ሰዎች ልዩነት ለሚያውቅ ሰው በሰሞኑ ከሃጫሉ ግድያ ጋር በሁለተኛ ዙር የተያዙትን ተጠርጣሪወች ወንጀለኛ ብሎ መፈረጅ እየሰሩበት ያለውን የስልጣን ወሰን(scope of jurisdiction) ካለማወቅ በተጨማሪ ተራ ፖለቲከኛ መሆንንና ለህግ ያላቸውን ሽፍትነት ያሳብቃል። አንድን ተጠርጣሪ ወንጀል ስለመፈፀሙ በወንጀል ክሶ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ(beyond reasonable doubt) በሆነ ማስረጃ አስረድቶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሳያስብሉ ወንጀለኛ ብሎ መፈረጅ ትልቅ አላወቂነት ነው።

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት ቁ ጥር 27 መሰረት አንድ ተጠርጣሪ በፖሊስ ጣቢያ ቃሉን ሲሰጥ የወንጀል ድረጊቱን ስለመፈፀሙ ሊያምን ወይም ሊክድ ይችላል ።በዚህ ወቅት አንድ ተጠርጣሪ በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ፣በስጋትና በጭንቀት ወስጥ ሆኖ፣ዝም የማለት መብቱ ሳይነገረው፣ጠበቃወን ሳያማክር የሚሰጠውን ቃል ብቻ በመወሰድ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አምኖ የሚሰጠውን ቃል ብቻ በመውሰድ እንደ ወንጀለኛ መቁጠር በየመገናኛ ብዙሃን ጣቢያዎች በመውጣት መለፈፍ የተጠርጣሪውን መብት ከመጣስና ትክክለኛ የድርጊቱን ፈፃሚ እንዳይታወቅ ከማድረጉ በተጨማሪ ነገ ከነገ ወዲያ ፍርድ ቤት ለሚሰጠው ውሳኔ ገልተኝነትና ታማኝነት አሉተሰዊ ተፅዕኖው ከፍተኛ ነው።

በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ አይደለም በወንጀለኛ መቅጫ ህገ ስነስርዓት ቀጥር 27 በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ ቃልን፣ በተመሳሳይ ህግ ቁጥር 35 መሰረት በፍርድ ቤት የተሰጠ ቃልም ቢሆንም እንደ አንድ ማስረጃ ከሚቆጠርና ከሚመዘን በስተቀር ብቻውን ቆሞ አንድን ተጠርጣሪ ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችል ባለመሆኑ፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ አቅርቦ ተጠርጠሪን በተገቢዉ የፍርድ አካሄድ በማሳለፍ(due process of law) በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ማስባል ይገባል እንጅ፣ ተከሰሹ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠውን ቃል ብቻ በመውሰድ ና የደረጃ ምስክር አለ እያሉ ተጠርጣሪን ከፍርድ በፊት ወንጀለኛ አድርጎ መፈረጅ፣ የወንጀሉ አፈፃፀም ውስብስብ ከመሆኑ አንፃር ጥንቃቄ ሳይደረግበት በማንአለብኝነት የሚወሰን ከሆነ ትክክለኛውን የድርጊቱ ፈፃሚ ማወቅ አይቻልም።

ሌላዉ ጠቅላይ ዓቃቢ ህጓ በመግለጫቸው የተናገሩት ጉዳይ "ከዚህ በኋላ በሽምግልና የሚፈታ ጉዳይ የለም" ብለዉ ማንሳታቸው እና በጥቅምት ወር 2012 ዓም የተፈፀመው ድርጊትም አብሮ እግረመንገዱን የሚጣራ መሆኑን ሲሆን ከዚህ የምንረዳው ለጥቅምቱ የወንጀል ድርጊት ተጠያቂ የነበረ ሰው አሁንም በተመሳሳይ ድርጊት ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው መኖሩንና ከዚህ በፊትም ቢሆን የወንጀል ድረጊት ተፈፅሞ በሽምግልና የተቋረጠ ጉዳይ መኖሩን መገንዘብ ይቻላል። የወንጀል ድርጊት እንዲፈፀምና የንፁሃን ዜጎች ህይወት እንዲጠፋ ምክንያት የሆነን ሰው ጉዳይ በሽምግልና ከፈታችሁና የህግ ማዕቀፉን ከዘነጋችሁት ፣አሁንም ቢሆን የህዝቡን ስነልቦና

ከተረዳችሁ በኋላ ና ጉዳዩ እየተረሳ ሲመጣ "ለህዛብ ጥቅም" ብላችሁ ይቅርታ ወይም ምህረት የምታደርጉ ከሆነ በንፁሃን ዜጐች ደም የፖለቲካ ቁማር መቆመር ነው።

በመሆኑም መንግስት ለፖለቲካ ጥቅም ብቻ ሲል ያሰራቸውን እስክንድርንና የባልደራስ አባላትን ከእስር እንዲፈታ፣ በፖሊስ ለታሰሩ ዜጎች ፈጣን የሆነ የፍርድ አካሄድ እንዲሰጣቸው፣የፍትህ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጡ፣የዜጎች ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት እንዲከበር፣የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ ተጠርጣሪዎችን ከጥፋተኝነት ፍርድ በፊት ጥፋተኛ አድረጎ የፈረጀውን ፍረጃ ይቅረታ እንዲጠይቅና ወደፊትም መሰል ድረጊት ከመፈፀም እንዲቆጠብ፣ በኦሮሚያ ክልል በማንነታቸው ምክንያት ህይዎታቸውን ላጡ ዜጎች ቤተሰቦች መንግስት ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ተገቢዉን ድጋፍ እንዲያደርግና በክልሉ ለተፈፀመው አስነዋሪ ተግባር መንግሰት ሃላፊነቱን ወሰዶ ወደፊት ተመሳሳይ ድረጊት እነዳይፈፀም ያለበትን ግዴታና ሃላፊነት እንዲወጣ በአንክሮ እጠይቃለሁ።

**አራጋው ሲሳይ ደመቀ /ቶሮንቶ/ ካናዳ**

**በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ ቢሮ ዓቃቢ ህግ**

**ሃምሌ 2012 ዓም**